መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
አቅራቢዎች

# ኢየሱስ አይነ ስውሩን ፈወሰ



ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest

ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Henok Estifanos

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2020 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፥- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

በርጤሜዎስ አይነ ስውር ሰው ነበር፤በኢያሪኮ አጠገብ በመንገድ ዳር ይቀመጥ ነበር፡፡ይለምን ነበር፡፡አንዳንድ መልካም ሰዎች ትንሽ ሳንቲም ወይም ቁራሽ ምግብ ሲያልፉ ይሰጡት ነበር፡፡ በርጤሜዎስ መስራት አይችልም ነበር ምክንያቱም ማየት አይችልም ነበርና፡፡እርሱ ማድረግ ይችል የነበረው መለመን ብቻ ነበር፡፡



አንድ ቀን መንገዱ በሰው ተጨናንቆ ነበር፡፡በርጤሜዎስ የብዙ ሰው የእግር ኮቴ ሰማ፡፡አንድ ያልተለመደ ነገር እየሆነ ነበር፡፡ ወዲያው አይነ ስውሩ ሰውዬ ምን እንደሆነ አወቀ፡፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ በከተማ ውስጥ ነበር፡፡በርካታ ህዝብ ኢየሱስን ለማየት እና ለመስማት ተሰብስበው ነበር፡፡





"ኢየሱስ፤የዳዊት ልጅ፤ማረኝ!"
በርጤሜዎስ ለምን ጮኸ? እርሱ
ኢየሱስ ሊረዳው እንደሚችል ለምን
አሰበ? ምናልባት ኢየሱስ
ስለፈወሳቸው ሌሎች ሰዎች ሰምቶ
ያውቅ ይሆናል? አንዳንዱ መስማት
የማይችሉ ነበሩ፤አንዳንዱ ደግሞ
መናገር የማይችሉ ነበሩ፤ሌሎች
ደግሞ መሄድ የማይችሉ ነበሩ -
አንዳንዱ ደግሞ እንደ እርሱ አይነ
ስውራን ነበሩ፡፡ "የዳዊት ልጅ፤ማረኝ"
እያለ በርጤሜዎስ ደጋግሞ ጮኸ፡፡
ድምጹ በተስፋ የሚደውል ነበር፡፡



በርጤሜዎስ በአንድ ነገር ላይ
እርግጠኛ ነበር፡፡አሁን እርዳታ
የማያገኝ ከሆነ፤ሌላ እድል
ላያገኝ ይችላል፡፡ኢየሱስ
እንደገና በመንገዱ መቼም
ላያልፍ ይችላል፡፡



በርጤሜዎስ ኢየሱስን ማግኘት አለበት፡፡ነገር ግን ህዝቡ አልተንቀሳቀሰም፡፡ "ሸሸሸሸሸሸ!" አሉት፡፡ ጸጥ እንዲል አስጠነቀቁት፡፡



ነገር ግን በርጤሜዎስ ጸጥ አላለም፡፡ መጮኹን ቀጠለ እንጂ፡፡ድንገት ኢየሱስ ቆመ! ሰማ! አይነ ስውሩን ሰውዬ ወደ እርሱ እንዲያመጡት አዘዘ! "አይዞህ!" ተነስ፡፡ይጠራሃል ብለው ለበርጤሜዎስ ነገሩት፡፡



ልብሱን እየወረወረ፤በርጤሜዎስ ተነስቶ ወደ ኢየሱስ ሮጠ።



"ምን እንዳደርግልህ ትወዳለህን?"ብሎ ኢየሱስ ጠየቀው፡፡ እንዴት ነበር የምትመልሱት? በርካታ ገንዘብ፤ወይም አዳዲስ ልብሶችን ትጠይቁ ነበር? በርጤሜዎስ ይፈልግ የነበረው ያንን ነውን?



አይደለም፤ዓይነ ስውሩ በርጤሜዎስ ኢየሱስን
ወርቅ ወይም ጥሩ ልብሶችን አልጠየቀም፡፡
ምን ይፈልግ እንደነበር
ታውቃላችሁ፡፡



"ጌታ ሆይ አይ ዘንድ" በርጤሜዎስ ይፈልግ የነበረው ማየት ነበር! ዛፎችን
እና ወፎችን እና ውብ የሆኑትን የእግዚአብሔር
ፍጥረታት ማየት፡፡ እርሱ መለመን ሳይሆን
ራሱን ችሎ መኖርን
ማየት ይፈልግ
ነበር፡፡



ከዚያም ኢየሱስ በርጤሜዎስን "እይ፤አምነትህ አድኖሃል" አለው፡፡



አንድ ጊዜ ማየት ከቻለ በኋላ ኢየሱስን ተከተለው፡፡እሱ ሊናገር የቻለው "እግዚአብሔር አስደናቂ ነው!" እርሱ ፈውሶኛል!" የሚል ብቻ ነበር፡፡

ለበርጤሜዎስ

አስደናቂ

ጊዜ ነበር፡፡





ሁሉም ሰው ይህን ባየ ጊዜ
እግዚአብሔርን አመሰገነ፡፡
እንደገና፤ለድሃው አይነ ስውር
ለማኝ ብርሃን ሲሰጥ አስደናቂ
የሆነውን የእግዚአብሔር ልጅ
የኢየሱስን ኃይል ተመለከቱ፡፡

ኢየሱስ አይነ ስውሩን ፈወሰ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ማርቆስ 10, ሉቃስ 18, ዮሐንስ 9

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝነት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16